# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአብየተ ክርስቲያናት ሕብረት ኮንፍራንስ

በችካጎና አካባቢው የተዘጋጀ ታላቅ ኮንፈረንስ በ August 18 (7 p.m.), August 19 (2 p.m.) እና August 20 (1:30 p.m.) በችጋጎ የምስራች ቤተ ክርስቲያን ይደረጋል። በዚህ ኮንፈረንስ ላይ ፓስተር መስፍን ሙሉጌታ ከኢትዮጲያ ያገለግለናል። እባካችሁ ሰዎችን ጋብዙ። ጌታ ይባርካችሁ።

### የገንዘብ ማሰባሰቢያ ቅጽ

ለሕንጻ ግዢ የገንዘብ ማሰባሰቢያ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልታችሁ ያልመለሳችሁ ወገኖች እባካችሁ ሞልታችሁ ለዲያቆናት ስጡልን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

### የአርብ ፕሮግራም

የአርብ ፕሮግራም የምጸልይበት፣ የምንንቃቃበትና የምንማርበት ፕሮግራም ነው። የምንችል ሁሉ እንድንካፈል እናበረታታለን። ጌታ ይባርካችሁ!

*“በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፥ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።” (ኢሳ. 27፡6)*



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ **Yeec.org App** ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2፡10




“ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ፤ አመስግኑት፥ ስሙንም ባርኩ።”
(መዝ. 100፡4)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**August 6, 2017**

**ሐምሌ 30፣ 2009 ዓ.ም.**

## የእለቱ ፕሮግራም መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | ወንድም ሰለሞን ዴሌቦ |
| አምልኮ..................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ቃል ........................... | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

"ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ ከጠላቶቼም እድናለሁ።"
(2ሳሙ. 22፡4)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 6602 N. Damen Ave., Chicago IL 60626 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ማክሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ዴሌቦ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ምስጋና — የድል መንገድ

*"ምስጋና የሚሠዋ ያከብረኛል፤ የእግዚአብሔርን ማዳን ለእርሱ የማሳይበት መንገድ ከዚያ አለ።" (መዝ. 50፡23)*

ምስጋና እግዚአብሔርን የምናከብርበት መንገድ ነው። ምስጋናችን በፊቱ እንደሚያርግ መስዋዕት ለእግዚአብሔር የመአዛ ሽታ ነው። በምስጋና ውስጥ ደግሞ የደህንነት መንገድ አለ። እግዚአብሔርን ምስጋናን ለሚሰዋ ማዳኑን፣ ምህረቱን፣ እርዳታውን ይለግሳል። ምስጋና ዘርፈ ብዙ ነው፤ በዋናነት ግን ስናመሰግን ሶስት ነገሮችን እንዳደርጋለን።

(1) **ስናመሰግን እግዚአብሔር ላደረገልን ነገር እውቅና እየሰጠን ነው፡-** እግዚአብሔር ከቁጥር በላይ የሆነ ነገር አድርጎልናል። መዳናችን ቀዳሚ ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እኛ ሁላችን ሙታን ነበርን። ደግሞም በጨለማ ነበርን። ሕይወትን ያውም የዘላለም ሕይወት ስለሰጠን ሁልጊዜ ልናመሰግነው ይገባናል። በጨለማችንም ላይ ታላቅ ብረሃን በርቷል። መዳን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጆችም ሆነናል። ልጅነታችን ውስጥ ብዙ የከበረ ነገር አለ። ልጅነታችን ውስጥ የእግዚአብሔር አባትነት አለ፤ የእግዚአብሔር ፍቅር አለ፤ ወደ እርሱ አለመከልከል መቅረብ አለ እንዲሁም በእርሱ ደስታ ውስጥ መግባት አለ። ልጆች ብቻ ሳይሆን ያደረገን ደግሞም ለአገልግሎት ሾሞናል። በፊቱ ጉድ፣ ጉድ የምንል ባለማረጎች ተደርገናል። የክህነት ቅባት ፈሶብን፤ የክህነት ልብስ ለብሰናል። በምድር ሕይወታችንም ባርኮናል። ብዙ የምንቆጥራቸው በረከቶች አሉን። ታዲያ ይህንን ሁሉ ላደረገልን ጌታ ነብሳችን ማመስገን እና ውለታውን መቁጠር አለባት። ይህ እግዚአብሔርን ማክበር ነው።

(2) **ስናመሰግን የእምነት ቋንቋ እየተናገርን ነው፡-** በምስጋና ውስጥ እምነት አለ። የሚያመሰግን ሰው ከሁኔታዎች ሁሉ በላይ እግዚአብሔርን ከፍ ያደርጋል። አንዳንድ ጊዜ የምናልፍባቸው ሁኔታዎች ለማመስገን ላይመቹ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ይመሰገናል። እማባቆም እንደተቀኘው የበረቱ ቦዶ መሆን፣ የእርሻው መጉደል ምስጋናንን መቀነስ የለበትም። በዚያም ውስጥ እርሱ ጌታ ነው። ጳሎስና ሲላስ በወህኒው የውስጠኛው ክፍል ምስጋና ሲሰው የእምነትን ቋንቋ እየተናገሩ ነበር። ከእስራቱና ከእንግልቱ እግዚአብሔር ይበልጣል እያሉ ነበር።

(3) **ስናመሰግን በጠላታችን ላይ መንፈሳዊ ውጊያ እየከፈትን ነው፡-** እግዚአብሔር ሲመሰገን ጠላት ይዋረዳል። ዳዊት እንደ ዘመረው ከአፋችን የሚወጣው ምስጋና ቁመኛ የሆነውን ጥላታችንን ዲያቢሎስን ይመታዋል። (መዝ.8፡2) ምስጋናና መንፈሳዊ ውጊያ ጎን ለጎን ናቸው። የእግዚአብሔር ህዝብ ምስጋና "በጉሮሮአቸው ነው፤ ሁለት አፍ ያለውም ሰይፍ በእጃቸው ነው።" (መዝ. 149፡ 6) ምስጋና ሲቀድም ጠላት ይመታል።

ወገኖቼ፡- ለእግዚአብሔር የምስጋናን መስዋእት እንሰዋ እንጂ እንደ ዘጠኙ የዳኑ ለምጻሞች ምስጋናን የምናጓድል አንሁን። ምስጋናችን እጁን ታንቀሳቅሳለች—ማዳኑን ታመጣለች።